




# አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

**Melaku Kebede [LL.B, LL.M]**
**2024**

# ግጭት/አለመግባባት

- ግጭት/አለመግባባት ምንድን ነዉ?
- ስለ ግጭት ስታስቡ በአእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድን ነው?
- የግጭት መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
- የግጭት መንስኤዎችን ማወቅ ምን ጥቅም አለው?

# የግጭት መንስኤዎችን ማወቅ ምን ጥቅም አለው?

- አለመግባባቶችን በትክክል መረመርን ማለት እንዴት እንደምናስተዳድር ወይም እንደምናፈታው ተገቢውን መንገድ እንድንከተል ስለሚረዳን ነው።
- አለመግባባት እና ግጭት ተመሳሳይ ናቸው ?

# አለመግባባቶች እና ግጭቶች ተመሳሳይ ናቸው ?

- Are ***disputes*** and ***conflicts*** the same thing? Some scholars use the terms interchangeably, while other see important differences between the two.
- Social scientists are more likely to study “conflicts”, while those with legal trainers may focus on “disputes”.
- **Disputes** are often short-term disagreements.

# CAUSES OF CONFLICT

- Christopher Moore የተሰኘው ስኮላር የግጭት መንስኤዎችን በአምስት መደቦች መድቦ እናገኘዋለን እነዚህም፡-
- የግንኙነት ግጭት፣ የመረጃ ግጭት፣ የእሴት ግጭት፣ የመዋቅር ግጭት እና የፍላጎት ግጭት በማለት ይከፋፍላቸዋል ወይም “Circle of Conflict” (or sometimes “Moore’s Pizza”) ይሰኛሉ

## የግንኙነት ግጭት

- ከተሳሳተ ግንኙነት
- ከከባድ ስሜታዊነት
- የብልህነት ችግር
- ተደጋጋሚ አሉታዊ ባህሪ

## የውሂብ/የዳታ ግጭት

- የኢንፎርሜሽን/የመረጃ እጥረት
- የተሳሳተ መረጃዎች
- በመረጃ አግባብነት ላይ የተለያዩ አመለካከቶች እና
- ዳታ በተገቢው መንገድ የመተርጎም ችግሮች

## የእሴት ግጭት

- የህይወት መንገዶች ፣ ርዕዮተ ዓለም፣ የአለም እይታና ወዘተ..መለያየት
- አመለካከቶችንና ሀሳቦችን ለመገምገም የተለያዩ መስፈርቶች መኖር

## የመዋቅር ግጭት

- እኩል ያልሆ ስልጣን
- እኩል ያልሆነ የሀብት ቁጥጥር
- የጊዜ ገደቦች

## የፍላጎት ግጭት

- በፍላጎት ላይ የተነሳ ግጭት
- የአሰራር ፍላጎት ችግር
- በሳይኮሎጂ የተነሳ የሚመጣ የፍላጎት ችግር

# የግጭት ተዋናዮች/ CONFLICT ACTORS

1. **Conflict Actors or Parties**: Actors are those parties (individuals, groups or agencies) in a position to alter conflict dynamics.

a) ዋና ተፎካካሪዎች/ተዋንያን ***Primary contenders/actors***

b) አጋሮች/ደጋፊዎች /***Play as actors and allies***

c) የግጭት አማላጆች ***Conflict intermediaries*** –mediators, and all those attempting to facilitate resolution

# ግጭትን መመርመር/ DIAGNOSING CONFLICT

1. የግጭት መንስኤ የሆነውን ነገር በፈጠራ እና በማስተዋል መመርመር፣

2. ግጭቱን ለመፍታት በጥራት እና በብቃት እርምጃ መውሰድ፣ እና

3. ሁኔታው እንዳይባባስ ደካማ ምርመራ ላይ አለመመርኮዝ እና ጠንካራዎቹን በመለየት መተግበር

# ግጭት፡-

- ግጭት የሰው ልጆች አንዱ የህይወት ገጽታ ነው
- ግጭት በአግባቡ ተይዞ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል፡፡በአግባቡ ያልተዘ ግጭት(unmanaged conflict) ውጤቱ ጎጂ ነው፡፡
- ጉዳቱም ከንብረት ውድመት እስከ ክቡሩ የሰው ህይወት መጥፋት ሊያርስ ይችላል፡፡በተግባርም አገራችንን ጨምሮ በአለም ሊይ እየሆነ ያለው ይሄው ሀቅ ነው፡፡
- **ስለዚህ ግጭት መኖሩን ካመንን የግጭት መፍቻ መንገዶቹንም ቀድሞ ማበጀት ከምንም** በላይ አስፈሊጊ ነው፡፡
- በዚሁም መሰረት በዋነኛነት ሁለት አይነት የግጭት መፍቻ መንገድች አሉ እነሱም፡-
- **መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የግጭት መፍቻ መንገድች ይባላሉ፡፡**

## o **1ኛ. መደበኛ የግጭት መፍቻ መንገድ፡-**

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ግጭቶች ሲነሱ ቀድሞ በህግ በቀቋቋመ ፍርድ ቤት ወይም ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባላቸው አካላት እና በህግ በተዘረጋ ስርአት ውስጥ በማለፍ ግራቀኙን ወገኖች ቀርበው አቤቱታቸውን እና ምላሻቸውን አሰምተው በፍ/ቤት በተሰየሙ ዳኞች ግራቀኙን አከራክረው ተገቢ ነው ያለትን ውሳኔ የሚወስኑበት እና ይሄንኑ ውሳኔ የሚያስፈጽሙበት የግጭት አፈታት ስርአት ነው፡፡

**2ኛ. ኢ-መደበኛውን የግጭት አፈታት ስርአትን** ያየን እንደሆነ ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው እላይ ካነሳነው መደበኛ የግጭት አፈታት ውጭ ያለትን ሁለንም የግጭት አፈታት ዘዳዎች የሚያካትት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ **አማራጭ የግጭት አፈታት ስርአትም** ይባላል፡፡ይህም ስያሜ የተሰጠው በነባራዊው ሁኔታ ብዙ ጊዜ ግጭቶች በዋነኛነት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በሚደረግ ክርክር የሚፈቱ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ መደበኛው የግጭት አፈታት ስርአት በብዙ ምክኒያቶች ተመራጭ **የማይሆንባቸው** አጋጣሞዎች አሉ፡፡**የዚህን ግዜ አማራጭ የግጭት መፍቻ መፈለጉ ምክኒያታዊ** ነው፡፡ ለዚህም ነው አማራጭ የግጭት መፍቻ ስርአት የሚባለው፡፡

# አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

# ALTERNATIVE DISPUTE RESOLUTION

MELAKU K./LL.B, LL.M/

# MEANING

**Alternative Dispute Resolution /ADR/**

The word **Alternative** refers to:

- ❖ all permitted dispute resolution mechanisms other than litigation;
- ❖ It implies the existence of dispute settlement mechanisms other than formal litigation;

## ግጭት/DISPUTE IS:-

- *ግጭት ወይም ውዝግብ/a conflict or controversy;*
- *የይገባኛል ጥያቄዎች ወይም መብቶች ግጭት/conflict of claims or rights;*
- *an assertion of right, claim or demand;*
- *የክርክር ርዕሰ ጉዳይ /the subject of litigation;*
- ክስ ሊቀርብበትና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ

# Resolution may be understood as:-

- አለመግባባትን/ችግርን /ክርክርን፣ ውዝግብን ወዘተ...የመፍታት ሂደት ወይም የመፍታት ተግባር፣ /the act of resolving or ***settling*** a problem, dispute, controversy etc.
- በአጭሩ; ADR ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጪ ያለ የህግ አለመግባባቶችን የመፍቻ ዘዴዎች ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።

# የADR እድገትና በህግ የተሰጠው እውቅና

- አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ሂደቶች( ADR) በተግባር ከቆዩበት እድሜ በመነሳት ብዙውን ጊዜ ከጥንታዊ ባህላዊ ሂደቶች ብቻ ተያይዘው ቢቀርብም **ከ20ኛው ክፍለዘመን ወዲህ** ባህላዊና ሃይማኖታዊ አሰራሮች እንዲተገበሩ(legal pluralism) በመደንገግ ከሚወጡ **ህጎች፣ ከዘመናዊ የፍትህ ሂደትና የፍርድ ቤት አሰራሮች** ዘዴዎቹ ተቀባይነት አግኝተው ፍትህን ለማስፈን እንደ አማራጭ በመቅረብ የፍርድ ቤትን ስራ እያገዙ ይገኛሉ
- አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች በተለይ ድንበር ተሻጋሪ ንግዶችንና የንግድ ነክ ክርክሮችን ከመፍታት አኳያ ያላቸውን ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው
- ለዚህም የአማራጭ ሙግት ምፍቻ ትግበራ በሀገራት እንዲኖር ለማስቻል **የተባበሩት መንግስታት የአለም አቀፍ የንግድ ህግ ኮሚሽን(United Nations Commission on International Trade Law)** ሞዴል ህጎች አውጥቷል
- በተመሳሳይ በግልግል የተደረጉ ውሳኔዎችን በሌላ ሀገር ለማስፈጸም የሚያግዝ በተለምዶ **የኒዮርክ ስምምነት** በመባል የሚታወቀው ዓለም አቀፍ **ስምምነት (New York Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards,(1958)** ስራ ላይ ከዋለ በኋላ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት የሚፈቱበት ቁጥር ያደገበትና ዘርፉ ዘመናዊና ተመራጭ እየሆነ የመጣበት ሂደት ታይቷል፣
- በ1950 በጸደቀው የኒውዮርኩ ስምምነት እውቅና ያለው ሲሆን አገራችንም ይሄንን አለማቀፍ ስምምነት በህገመንግስቱ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ተቀብላ አጽድቃዋለች።

- ✓ በዚሁ ስምምነት መሰረት በሌላ የውጭ ሀገር የተወሰነ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የኢትዮጵን ህዝብ ሞራል ወይም ግብረገብነት እሴትን ማይጎዳ ከሆነ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱም በህጉ መሰረት ተከራካሪ ወገኖች በፈቃዳቸው በመረጡት ስርአት የተሰጠ ውሳኔ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተወሰነ ህጋዊ ውሳኔ ተቆጥሮ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡ **የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ውሳኔውን እውቅና ሰጥተው የማስፈጸም ስልጣን እና ሀሊፊነት አለባቸው፡፡**
- ✓ ከኒውዮርኩ ስምምነት በተጨማሪ በተባበሩት መንግስታት አለማቀፍ የንግድ ህግ ኮሚሽን በ**1986** የተዘጋጀ በንግድ አለም የግልግል ዳኝነቱ የሚመራባቸውን መርሆች ያካተቱ አለማቀፍ መርህ በዝርዝር የያዘ ሰነድ አውጥቷል እሱም **UNCITRAL model law on International commercial arbitration** በመባል ይታወቃል፣
- ✓ እነዚህ መርሆች አስገዳጅ ሳይሆኑ በተከራካሪ ወገኖች ነጻ ፈቃድ ላይ ተመስርተው በግልግል ጉባኤው ተግባር ላይ የሚውሉ መርሆች ናቸው፣

- ✓ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ በተመሳሳይ የግልግል ዳኝነት ወይም የሽምግሌና አሰራርን የሚዘረጋ አካል ተዋቅረል እሱም አለማቀፍ የኢንቨስትመንት ግጭት መፍቻ ማእከል **(international center for settlement of investment dispute(ICSID)** በመባል ይታወቃል።
- ✓ ይህ ማእከልም በአለም አቀፍ ቃልኪዳን የተቋቋመ ነው፣
- ❖ የሚቋቋሙት የግልግል ዳኝነት አካላት ቋሚ **(Permanent Arbitaration Tribunal )** ወይም ጊዜያዊ የግልግል ዳኝነት **(Adhoc Arbitaration Tribunal)** ሆነው ለየግጭቶቹ መፍትሄ ለመስጠት በየግዜው የሚዋቀሩ ሊሆኑ ይችሊለ። አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት ይሄንኑ ጊዜአዊ የግልግል ዳኝነት ሰጪ አካል ነው።

# አማራጭ የሙግት መፍቻ በኢትዮጵያ ያለው የህግ ማዕቀፍ

- በዋናነት መንግስት አማራጭ የግጭት መፍቻ ስርኣቶችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እውቅና በመስጠት የወንጀል ጉዳዮችን ከመደበኛው **የመንግስት ወንጀል ፍትህ ስርዓት**ጋር በማቀናጀት ለመፍታት እንዲቻል ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል፣
- በዚህም ዘመናዊው የፍትህ ስርኣት በኢትዮጵያ **በህገ መንግስትም እውቅና** በማግኘት በሌሎች ልዩ ልዩ **የወንጀል፣ የፍትሀብሄርና አስተዳደራዊ ህጎች** ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የተሰጣቸው ናቸው።
- ይሁን እንጂ ዘመናዊ የፍትህ ስርዓትና የህግ ማዕቀፎች ከመውጣታቸው በፊትም ቢሆን **የፍትሀነገስት፣ የሀይማኖት (ለምሳሌ በሸሪአ) እና በባህል ስርኣት ጉዳዮች** ሲስተናገዱና መንግስትም እውቅና በመስጠት እየተሰራባቸው ይገኛሉ፣

# 1. በኢ.ፌዲ.ሪ ህገመንግስት

- **የህገ መንግስቱ መግቢያ፣ በአለማነት ወይምም በግብ ደረጃ ካካተታቸው ጉዳዮች፡-**

- የቡድን መብቶች የሆኑት የባህልና የህይማኖት እኩልነትንና ያለ ገደብ መራመድን፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህን ማስፈን፣
- በሀገሪቱ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር ሲሆን
- ይህም አላማ/ ግብ/ ከሚሳካባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ በፍትህ ስርኣታችን ውስጥ የኢኮኖሚ ጉዳዮችን የተመለከቱና ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችሉ የውልና ሌሎች ግላዊና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በእኩልነት፣ፍትህዊነትና በህግ የበላይነት ማዕቀፍ ውስጥ በመተግበር አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ታሳቢ ያደረገ ነው፣
- ለዚህም በህገ መንግስቱ የብዝሀ ማህበረሰብ ህጎችንና ሀይማኖቶችን የተመለከቱ አደረጃጀቶችን እውቅና የሰጠና ድጋፍም እንደሚደረግላቸው ደንግጎ ይገኛል፣

- ✓ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶችን በፍርድ ቤቶችና ከፍርድ ቤቶች ውጪ ተፈጻሚ ከማድረግ ረገድ በሀገራችን የህገ መንግስትና የህግ ማዕቀፎች እውቅና የተሰጠው ከመሆኑ አንጻር በፍርድ ቤቶችና ከፍርድ ቤቶች ውጪ ተፈጻሚ የሚደረጉ በመሆኑ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9(1) መሰረትያልተከለከሉና ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው ፣
- ✓ የጋብቻ የግልና የቤ/ብ መብቶች በአንቀጽ 34 (4)(5).....በተከራካሪ ፈቃድ በሀይማኖቶች ወይም በባህል ህጎች መዳኘት...፣
- ✓ አንቀጽ 37(1) ..ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያግዙ በመሆኑ....እና በአንቀጽ 78(5)..የሀይማኖትና የባህል ፍ/ቤቶች እውቅና ማግኘት.. አንቀጽ 39፣88(2)፣48፣62(6) ..የብሄሮች የብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት መከበር ድንጋጌዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

# 2. በኢፌዴሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ

- በ2003 ዓ.ም መንግስት የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል። ይህ ፖሊሲም በውስጡ በርካታ ተራማጅና ችግር ፈቺ የህግ ፣የአሰራርና የአደረጃጀት ማዕቀፎች አቅጣጫዎችን በማመላከት ይዟል
- በፖሊሲው ውስጥ አንድን ጉዳይ ወደ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርኣት መርቶ ለመፍታት እንዲቻል ከግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚገቡ መርሆዎችን በዝርዝር ያስቀምጣል

# እነዚህ መርሆዎች፡-

1)የወንጀሉ አይነት፣

2)የተከሳሹ ባህሪ፣

3) ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታ፣

4)ከፍርድ ቤት ይልቅ የህዝብና የተጎጂው ጥቅም በአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት በተሻለ የሚጠበቅ ከሆነ፣

5) በግል አቤቱታ አቅራቢነት በሚታዩ ወንጀሎች በተጨማሪ ወጣት አጥፊዎች፣ሴቶች፣አካል ጉዳተኞች፣አዛውንቶች፣ደጋጋሚ ያልሆኑ፣ በቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የፈጸሙ አጥፊዎች፣በአጥፊውና በተጎጂው መካከል የእርቅ ስምምነት የተፈጸመ ከሆነ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርአት ሊስተናገዱ እንደሚችሉ ያስቀምጣል ( በአንቀጽ 4(6)2/1)፡፡

በአንቀጽ 4፣5፣6፣ ስር ደግሞ ስለ ጥፋተኝነት ድርድር ስርአት የደነገገ በመሆኑ የአማራጭ ሙግት መፍቻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

# 3. በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ

- በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ውስጥ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ክስ ተመስርቶባቸው በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የተደነገጉ ሲሆን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ውስጥም በአንቀጽ 216(2) ፤አንቀጽ13፤ 21(1)፤44(1)፣106፣ ከአንቀጽ 211-213 እንደተደነገገው ክሶች **በሁለት** መንገድ የሚቀርቡ እንደሆነና ይህም በአቃቤ ህግ ከሳሽነት እንዲሁም በክስ አቤቱታ አቅራቢነት/በግል አቤቱታ/ ቀርበው እንደሚስተናገዱ ይደነግጋል፣

- በዚህም በአንቀጽ 212 መሰረት በግል አቤቱታ አቅራቢነት ክስ ሊመሰረትባቸው በሚገቡ ወንጀሎች ላይ የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ የክስ አቤቱታ ሳያቀርቡ ክስ መመስረት እንደማይቻል ይደነግጋል፣

- በግል አቤቱታ ስለማቅረብ በተደነገጉት መሰረት **እነዚህን የወንጀል አይነቶች በእርቅና ሽምግልና አግባብ ለመፍታት እድል የሚፈጥሩ በመሆኑ** በትኩረት መሰራት የሚችልበት እድል እየፈጠረ ይገኛል፣

- በሌላም በኩል የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ በወንጀል ጉዳዮች የእርቅ አተገባበርን በተመለከተ ተፈጻሚ ለማድረግ መመሪያ ቁጥር **1/2012** በማውጣት በስራ ላይ ያዋለ ሲሆን በዚህም መመሪያ መሰረት በወንጀል ህጉ፣ በወንጀል ስ/ስ/ህግ፣ ወይም በሌላ ህግ ውስጥ በእርቅ ለማለቅ እንደሚችል የተጠቀሰ ማንኛወም ወንጀል እና ቀለል ያሉ የማህበረሰብ ጥቅምና ደህንነት የማይመለከቱ ለምሳሌ፡- በግል አቤቱታ አቅራቢነት በሚቀርቡ የወንጀል አይነቶች ባለጉዳዮቹን በማስታረቅ ሊያልቅ እንደሚቻል ይደነግጋል

# 4. የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት

- የወንጀል ጉዳዮች በመንግስት የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ከላይ እንደተገለጸው በሁለት መንገድ ቀርበው የሚስተናገዱ ሲሆን ይህም በቀጥታ የግል አቤቱታ/ክስ አቅራቢነት እና
- በአቃቤ ህግ ከሳሽነት ነው በዚህም መሰረት በአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርኣት ከማስተናገድ አንጻር የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርኣት ህግ በአንቀጽ 151(2) ስር ተሟጋቾች የግል አቤቱታ ባቀረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ተጎጂውን/ከሳሽን/ እና ተከሳሽን የማስታረቅ ስራ መስራት እንዳለባቸው ይደነግጋል፣
- በመሆኑም የወ/መ/ስ/ስ አንቀጽ 13 እና 21፣19-21፣42(1ሀ)፣44(1)፣47፣150፣151 ) ተፈጻሚነት አላቸው፣
- እንዲሁም በአንቀጽ 223 ስር አጥቢያ ዳኛ ቀላል ወንጀሎችን መዳኘት እንደሚችል ተደንገጎ ይገኛል፣

- በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ውስጥ በአንቀጽ 216(2) ፤አንቀጽ13፤ 21(1)፤44(1) ስር በግል አቤቱታ ስለማቅረብ በተደነገጉት መሰረት እነዚህን የወንጀል አይነቶች በእርቅና ሽምግልና አግባብ ለመፍታት እድል የሚፈጥሩ በመሆኑ በትኩረት መሰራት የሚችልበት እድል አለ ማለት ነው፣
- ይህም ጉዳይ በአዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ረቂቅ ህግ (በአንቀጽ 2/1/) ስርም ተካቶ ይገኛል።

# 5. በፍትሐብሔር ህግ

አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርአት በፍትሀብሄር ህጎች ውስጥ ተካቶ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ይህም በክርክር፣በውሳኔና በፍርድ አፈጻጸም ረገድ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፡-

- ✓በፍትሀብሄር ህግ ከአንቀጽ 3307- 3317/፣
- ✓የፍትህ ብሄር ስነ ስርአት ህግ፣
- ✓የተሸሻለው የኢፌዴሪ የቤተሰብ ህግ፤
- ✓የአሰሪና ሰራተኛ ህግ አዋጅ ቁጥር 1156/2012፣
- ✓የተሻሻለው የንግድ ህግ፣
- ✓የኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009፣
- ✓የማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002
- ✓የገጠር መሬት አዋጅ፣
- ✓የከተማ መሬት የሊዝ አዋጆች፣
- ✓የኢንቨስትመንት አዋጆች፣
- ✓የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013፣
- ✓የግልግል ዳኝነትና የእርቅ ስምምነት ስርአት አዋጅ 1237/2013፣
- ✓የይቅርታ አሰጣጥ ስነ ስርአት አዋጅና መመሪያዎች፣
- ✓የፍርድ ቤት መር አስማሚነት መመሪያ ቁጥር 12/2014 ተጠቃሽ ናቸው።

በአገር አቀፍ ደረጃ የግልግል ዳኝነትን የሚመራበትን እና ውሉ የሚፈጸምበትን ህግ በ1952 የፍትሀ ብሄር ህግ ከአንቀጽ 3325 እና ቀጥሎ ባሉት አንቀጾች የደነገገ ሲሆን የግልግል ዳኝነቱ ስርአት የሚከተለውን ሂደት ደግሞ በ1957 በወጣው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ ተደንግጓል።

# Discuss

i. በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች/INDIGENOUS DISPUTE RESOLUTION MECHANISM/ እና በዘመናዊ አ.የግ.አፈታት ዘዴዎች መካከል/ MODERN ADR/ መካከል ያለው ልዩነት ??
ii. የADR – አላማዎች ??
iii. ADR ADVANTAGES??
iv. ADR DISADVANTAGES??
v. DEMERITS (SHORTCOMINGS) OF LITIGATION?

| ባህላዊ/Indigenous Dispute Resolution Mechanism | ዘመናዊ/ Modern ADR |
|---|---|
| የቃል ቅሬታ/Oral Complaint/ | Written Complaint |
| ስሜታዊ - መደበኛ ያልሆነ ምላሽ/Emotional – informal response | Controlled – formal response |
| ተከራካሪዎች አብረው ይኖራሉ/Disputants live together | Disputants – often strangers |
| አብዛኛውን ጊዜ በሽማግሌዎች መዳኘነት/Usually a jury of Elders | ዳኛ ለመሆን የግድ ሽማግሌ መሆን አያስፈልግም/Occasionally a jury of peers |
| እድሜ እና ጥበብ ያስፈልጋል/Age and wisdom required | Recognition, experience and appointment required |
| No rules of evidence | Fixed rules of evidence |
| ሂደቱ ከክርክር ክርክር ይሻሻላል/Procedure evolves with dispute | Precise procedure |
| ተከራካሪዎች እና የተከራካሪ ቤተሰብ ተወካዮች የግልግል ዳኞችን ያነጋግራሉ Disputants and family representatives address arbitrators | ህጋዊ ተወካዮች ብቻ የግልግል ዳኞችን ያነጋግራሉ/Legal representatives address arbitrators |
| Time not an issue | Deadline Intensive |
| Informal culture | Court-annexed – formal culture |
| ከተከራካሪዎች ጋር ውይይት ይደረጋል/Settlement discussed with disputants | ፍርድ ለተከራካሪዎች ይተላለፋል/Judgement delivered to disputants [Arbitration] |

# አግአ - የሚከተሉትን አላማዎች ያሳካል፡-

- የፍትህ ተደራሽነት ያረጋግጣል - Art. 37 of FDRE C
- ተቀባይነት ያለው የፍትህ ሥርዓት ያግዛል
- የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች መብት ለማሳደግ እና ባህል ነክ ዓላማዎችን ለማሳካት ያስችላል  - Art. 39(2) ad 91(1) of FDRE C
- ከመደበኛ ፍ/ቤቶች አንጻር ሲታይ ግንኙነትን ያክማል

# ADVANTAGES OF ADR?

1) Speed;
2) Choice and expertise of impartial neutrals;
3) Informality and flexibility;
4) Privacy;
5) Economy;
6) Finality/ግጭትን ከፍጻሜ ያደርሳሉ;
7) Diversity and adaptability of ADR; /አማራጭነትና ተስማሚነት
8) Recognition of the needs of the parties;
9) Win-win situation;
10) Restorative
11) Qualitative improvement in the delivery of justice/በፍትህ አሰጣጥ ላይ የጥራት መሻሻል እንዲመጣ ያግዛል
12) Increased participation and access to justice.

# ADR DISADVANTAGES:-

1) **In balance of power**
2) **Lack of legal expertise**
3) **No system of precedent**
4) **Enforcement**

## DEMERITS (SHORTCOMINGS) OF LITIGATION፡-

1) **Cost of Litigation**
2) **Time**
3) **Litigation is Public**
4) **Absence of creative solutions**
5) **Little Opportunity for the Parties to voice Frustration/ውስን ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት**
6) **Unpredictability**
7) **Lack of Expertise of Decision Maker/የውሳኔ ሰጪ ባለሙያ እጥረት**
8) **Control over the Process/ በእያንዳንዱ ሂደቱ ላይ ቁጥጥር መደረግ**
9) **Win/Lose**
10) **Damage to Relation**
11) **Emotional Cost**

# የ ADR ምድቦች ፡-

በእያንዳንዱ የግ/አፈታት ዘዴዎች የምንከተላቸው ሂደቶችን መሰረት በማድረግ በሶስት ምድቦች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። እነዚህ ምድቦች የተመሰረቱት የግ/አፈታት ዘዴው የሚስገኘውን የውጤት ዓይነት እና ተዋዋይ ወገኖች እንዴት እንደሚሳተፉበት በማጤን ነው።

የ ADR ሂደቶች ምድቦች፡-

ሀ. የስምምነት ሂደት፣

ለ. የውሳኔ ሂደት እና

ሐ. የምክር ሂደት ናቸው፡፡

# ሀ. የስምምነት ሂደት/PROCEDURE OF AGREEMENT-

- እንደ **ድርድር፣ ሽምግልና** የመሳሰሉት ሁሉም የስምምነት ሂደቶች ናቸው፣
- የእነዚህ ሂደቶች የሚያመጡት ውጤት በተሳተፉት ሰዎች ስምምነት ላይ የተመሰረተ ነው፣
- ስምምነት ከሌለ ምንም ውጤት **አይጠበቅም፣**
- በዚህ የADR የስምምነት ሂደት ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች በግለሰብ ደረጃ ሊያመጡት ከሚችሉት ከማንኛውም ውጤት የላቀ ውጤት ለማምጣት በጋራ በመስራት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣
- በዚህ የስምምነት ሂደቶች negotiation, mediation, facilitation, partnering and mini-trial ይካተታሉ ።

# ለ. የውሳኔ ሂደት/PROCEDURE OF DECISION -

- የውሳኔ ሂደት - የግልግል ዳኝነት ዋነኛው ሂደት ነው፣
- ግጭቱ ወይም አለመግባባቱ እንዴት ይፈታል የሚለው ጉዳይ **በሶስተኛ ሰው ውሳኔ ላይ የተመረኮዘ የሚሆንበት ነው፣**
- በዚህ ሂደት ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ሂደቱን በማገዝ ወይም ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ በትብብር ሊሳተፉ ይችላሉ፣
- ነገር ግን በመጨረሻው የውሳኔ ሂደት በሚሰጥበት ወቅት **የተሳታፊዎቹ ሚናዎች** የሚሆኑት <u>በእጃቸው ያለውን ማስረጃ ፣ እውነታዎችን እና አግባብነት ያላቸውን ክርክሮችን በማቅረብ ብቻ የተገደቡ</u> ናቸው።

# ሐ. የምክር ሂደት/PROCEDURE OF ADVICE -

- የምክር ሂደት - በገለልተኛ አካል ጉዳይን ማስገምገም ወይም ቀደምት ገለልተኛ ግምገማ ማስደረግ ነው ፣
- አስገዳጅ ያልሆነ የግልግል ዳኝነት ፣ የእውነታ ፍለጋ ወይም ምርመራ እና የባለሙያ አስተያየት ሁሉም የምክር ሂደቶች ናቸው ።
- የእነዚህ ሂደቶች የሥራ ውጤት ተሳታፊዎችን ለማሳወቅ ወይም ለመምከር የታሰበ ነው።

# BUNDLES OF ADR/አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

A. **“ድርድር”/Negotiation**

B. **መስማማት/ግልግል/COMPROMISE**

C. **ዕርቅ/MEDIATION/ CONCILIATION**

D. **ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት/ Arbitration**

E. **ድብልቅ/Hybrid/**

F. **ፍርድ ቤት መር/Court-Annexed/**

# A)NEGOTIATION [ድርድር]

# A) NEGOTIATION/ስምምነት/ድርድር

- Negotiation – is a “mutual discussion and arrangement of terms of a transaction or an agreement” (Macquarie Dictionary, 2005).
- ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ፣ድርጅቶችና ተቋማት በሆነ ጉዳይ ባለመስማማት ወደ አልተፈለገ ጭቅጨቅና ግጭት እንዳያመሩ ይህንኑ ያልተስማሙበትን ጉዳይ ለጋራ ጥቅምና ደኅንነት ሲባል ቁጭ ብለዉ ሌላ **3ኛ ወገን ጣልቃ ሳይገባ** በስምምነት የችግሩ መነሻ በሆነዉ ጉዳይ ላይ መፍትሔ የሚያስቀምጡበት ዘዴ ነዉ

- የ“ድርድር” ዋነኛ ዓላማው አለመግባባቶችን በንግግር ወይም በውይይት መፍታት ላይ ያለመ የማግባቢያ ዘዴ መሆኑ ነው፤

- ድርድሩ ለግል ወይም ለጋራ ጥቅም ወይም የተለያዩ ፍላጐቶችን ለማርካት ታቅዶ ተደራዳሪዎች ራሳቸው በሚገኙበት ወይም በወኪሎቻቸው በሚወከሉበት የድርድር መድረክ ይከናወናል፣

- ድርድር በሀገራት በካከል፣ በንግድ ወይም ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች እንዲሁም በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ከሚያጋጥሙ አለመግባባቶች አንስቶ የግል አለመግባባትን በሰላም በመፍታት ጭምር ጥቅም ላይ ይውላል፣

- በድርድር ስምምነት የተጨረሰዉ ጉዳይ ዕድሜ ያለዉ፣ ሰላምን ይዞ የሚመጣ እና ለስምምነቱ መሰረት ሆነዉ ጉዳይም ወደ ኋላ የመመለስ ዕድሉም በጣም ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል

# የድርድር መሰረታዊ ነገሮች/ELEMENTS OF NEGOTIATION

- ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን ለመፍታት ይሞክራሉ፣
- ሂደቱ አብዛኛውን ጊዜ ለተዋዋይ ወገኖች ስልጣን ይሰጣል፣
- ሂደቱ ብዙውን ጊዜ በself-determination ላይ የተመሰረተ ነው፣
- ሂደቱ የግድ የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት አያስፈልገውም፣
- the parties generally control the process; and
- ተዋዋይ ወገኖች በአጠቃላይ እርስ በርስ የሚያረካ ውጤት ለማግኘት ይተጋሉ

# የድርድር ጥበብ/NEGOTIATION SKILLS

- ጥሩ የንግግርና የቋንቋ ክህሎት፣
- ግላዊት/ዘር፣ ቀልም፣ሀይማኖት ወዘተ../ እንዳይነኩ መጠንቀቅ፣
- አለመግባባት ሲፈጠር እረፍት ማድረግ፣
- ግጭትን ሊያባበስ የሚችሉ ነገሮችን አስቀድሞ መለየት፣
- የተደራዳሪ ባለጋራን አስተሳሰብ፣ ሐይማኖትና ባህል ጠንቅቆ ማወቅ፣
- በውይይት ወቅት ከጠብ አጫሪነት መጠንቀቅ፣ ትህትና ቃላት መጠቀም፣
- የተደራዳሪ ባለጋራን ሃሳብ ከልብ መስማት፣
- ብዙ አማራጭ ሃሳቦችቸ ማመንጨት፣
- ተደራዳሪ ባለጋራን ማክበር፣
- የግንኙነት አድማስ የማስፋት ክህሎት ማዳር ወዘተ...ናቸው

# ADVANTAGES OF NEGOTIATION

- ተዋዋይ ወገኖች ሂደቱን በራሳቸው ምምራት መቻላቸው እና ውሎቻቸውን በፍላጎታቸው አዘጋጅተው ስምምነቶቻቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ
- ሁሉም ፓርቲዎች በአሸናፊነት ቦታ ላይ የመድረስ እድል አላቸው/ reaching win-win position
- አለመግባባቱ ባይፈታም ተዋዋይ ወገኖች ከፍርድ ቤት ችሎት በፊት ጉዳዮቹን ለማጥበብ እድሉ አላቸው።

# የድርድር ሞዴሎች /MODELS OF NEGOTIATION

1) **የትብብር ድርድር/Cooperative/Integrative-N**
2) **ተወዳዳሪ ድርድር/ Competitive/Adversarial-N**
3) **በመርህ ላይ የተመሰረተ ድርድር /Principled-N**
4) /Distributive-N

# 1) COOPERATIVE-N /የትብብር ድርድር/

- ለጋራ ጥቅም መሰረት ማድረግ፤
- ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አካሄዶችን ይጠቀማል
- ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ወገኖች አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ጉዳዮች ይደራደራሉ
- ፓርቲዎቹ ጥብቅ /strict/ ተወዳዳሪዎች አይደሉም

# 2)COMPETITIVE/ADVERSARIAL–N/ተወዳዳሪ ድርድር/

- የጋራ ጥቅም ከማግኘት ይልቅ **በማሸነፍ** ላይ አፅንዖት በመስጠት ይታወቃል
- ድልን ከፍ ለማድረግ ይፈልጋል/Seeks to maximize victory
- Adversarial **N**– characterized as zero sum game – win-lose
- ይህ የሚያመለክተው አንዱ ወገን ሲያሸንፍ ሌላኛው ሲሸነፍ የተወሰነ መጠን ያለው ትርፍ ወይም ኪሳራ ሲኖር ነው። በዚህም ተሸናፊው ፓርቲ የአሸናፊውን ፓርቲ ጥያቄ ከመቀበል ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም



# 3) PRINCIPLED NEGOTIATION/በመርህ ላይ የተመሰረተ ድርድር

- Most popular model
- በዋናነት በግጭት አስተዳደር እና በግጭት አፈታት ላይ የሚያተኩር ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የድርድር አቀራረብ ነው
- በመርህ ላይ የተመሰረተ ድርድር ሲሆን ከአቋማቸው ይልቅ የሁሉንም አካላት ጥቅም ላይ የሚያተኩር የድርድር አካሄድ ነው። ግቡ ለጋራ የሚጠቅም ውጤት ማግኘት ነው
- Developed by Fisher and Ury - **የተደራዳሪዎችን አቋም በማየት ተደራዳሪው ምን ይፈልጋል/ምንድነው የሚፈልገው ከሚለው ወደ በምን ይቋጫል በሚለው ላይ የተመሰረቱ ተደራዳሪዎች ይጠቀሙበታል**
- ዘላቂ ውጤት በሚያመጣ ድርድሮች ላይ ትኩረት ይደረጋል



# 4) የድልድል ድርድር/Distributive-N

- የዚህ ድርድር ልዩ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ተዋዋይ ወገኖች ሌላውን ወገን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ከፍተኛውን ጥቅም መፈለግ ነው
- በድርድሩ ውስጥ የተሳተፉ ግለሰቦች ለእነሱ የሚጠቅም ምርጥ አቅርቦት ይፈልጋሉ
- ቋሚ ሀብቶችን ለማግኘት ፍላጎት ያላቸውን ሁለት ወገኖች የሚካተቱበት ሆኖ አሸናፊ-ተሸናፊ ሁኔታ የሚያመጣ /a win-lose situation/ወይም የዜሮ ድምር ጨዋታ ይታይበታል



# ህጋዊ ውጤቶች/LEGAL EFFECTS OF NEGOTIATION AGREEMENT:-

- በድርድሩ ተዋዋይ ወገኖች ሕጉ ለውሎች ያስቀመጠውን መስፈርቶች እስካከበሩ ድረስ ሕጋዊ ውጤት አለው። ህጉ ገደብ ያሚያስቀምጠው የድርድርን ሂደትም ሆነ የሚቀርጹ ህጎችን ይዘት ብቻ ሳይሆን በተደራዳሪ ወገኖች ላይ ጭምር ተፈጻሚነት አለ
- በአንዳንድ ሁኔታዎች ህጉ የድርድር መቋቋምን ይከለክላል።

  ምሳሌ፡_ስምምነቱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ወገኖች ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ የሚጠይቅበት ወይም ባልተጠናቀቀ ስምምነትውስጥ እንዲገቡ ወይም ሌላ የንግድ እንቅስቃሴን የሚገድብ ሲሆን ነው።
- ስምምነቱ በተደራዳሪ ወገኖች መካከል እንደ ህግ ይቆጠራል በእነሱ ላይም አስገዳጅ ይሆናል።

# B) COMPROMISE

## [መስማማት/ግልግል/]

MELAKU K./LL.B, LL.M/

# COMPROMISE/መስማማት

- መስማማት ማለት ሰዎች በመካከላቸው የተፈጠረውን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችልለ ክርክር ለማስቀረት ወይም ለመተው የሚያደርጉት የጋራ ስምምነት የሚፈጠር ውል ነው።
- Art. 3307; 1678, 3308 of the CC and Art. 274 of Civ. Pr. Code applies

- ተዋዋይ ወገኖች በወቅቱ ወይም ለወደፊቱ በሚያፈሯቸው ጥቅሞች ላይ አለመግባባት ቢያጋጥም አለመግባባቱን በሶስተኛ ወገን ሙያዊ ወይም የቴክኒክ ዕገዛ ለመፍታት በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት የሚከናወን ሌላው አማራጭ የግጭት አፈታት ስልት ነው፤
- አስታራቂው አለመግባባቱን ለመፍታት ባለጉዳዮችን በተናጠል በማነጋገር የማስታረቂያ ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
- ከሽምግልና ፤"ዕርቅ" የሚለይበት አንዱ መሠረታዊ ነጥብ አስታራቂው ሁለቱንም ባለጉዳዮች ግንባር ለግንባር እንዲያገናኝ የማይጠበቅበት መሆኑ ነው፤
- ነገር ግን እያንዳንዱን ተዋዋይ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በተናጠል ማነጋገር እና የደረሰበትን ውጤት ለባለጉዳዮቹ መግለፅ እንዲሁም በሚያገኘው ግብዓት አለመግባባቱን መፍታት የሚያስችል የዕርቅ ሃሣብ (proposal) በፅሁፍ አዘጋጅቶ በማቅረብ ላይ የተመሠረተ ግዴታ አለበት፤

- አስታራቂው በሚያቀርበው ሰነድ ላይ ባለጉዳዮቹ ከተስማሙ በሰነዱ ላይ እንዲፈራረሙበት ይደረጋል፡፡ ስለሆነም በሰነዱ ላይ የሰፈሩትን ግዴታዎች እንዲፈፅሙ ይገደዳሉ፣
- በዚህ ረገድ በተለይም የግልግል ተግባር በውጤት ሲታይ አስገዳጅ ተፈፃሚነትን ስለሚያስከትል ከድርድር እና ከሽምግልና የተሻለ ዉጤታማ ነዉ ተብሎ ይገመታል
- በአንፃሩም ደግሞ በግልግል ዳኝነት እንደሚታየው የፍ/ቤቶችን አሰራር ስለማይከተል እና የዕርቅ ሰነዱ በተዋዋዮች ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት የሚደረግለት ህጋዊ ጥበቃ ስለማይኖር፣ "ዕርቅ" ከግልግል ያነሰ ተቀባይነት አለው ተብሎ ይገመታል፣

# COMPROMISE

**Art. 3313 – Void/False Document – Fundamental/**ዋነኛ ፡ ስሕተት

1) ፍርስ ወይም ሐሰተኛ የሆኑ ሰነዶች

2) ከስሕተት፡ የተነሣ፡ ግልግልን፡ ለማፍረስ/invalidation/ የሚቻለው ለመፈጸም ፡ ግዴታ የገቡበት ፡ ሰነድ ፡ ራሱ ፡ ፍርስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ነው

3) እንዲሁም ፡ የተዋዋይ ወገኖች፡ ወይም፡ ከነርሱ፡ ያንዱ፡ ፈቃድ የተገኘው, ሐሰተኛነቱ ፡ በታወቀ ፡ ባንድ ፡ ሰነድ ፡ መሠረት እንደ ሆነ ግልግሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል

4) በውሉ ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ሰነዱ ፈራሽ ወይም ሐሰተኛ ለመ ሆን ፡ መቻሉን ፡ አስበው ፡ የተገላገሉ፡ እንደ ሆነ በሁለቱም ጊዜ ግል ግሉ፡ እንደ፡ ጸና ፡ ይቀራል

# COMPROMISE/ስምምነት

**Art. 3316 – Illicit Object /**ህገ ወጥ የሆነ ግብ

**ግልግሉ ለህግ ወይም ለመልካም ተግባር ተቃራኒ** ከሆነ በአንድ ውል የጋራ ግንኙነት ያለው እንደሆነ ፍርስ ነው /A Compromise relating a contact **the object** of which is **contrary to the law or to public morality shall be of no effect**

እዚህ አንቀጽ 3316 ሌላኛው የአንቀጽ 1714 - 1716 ሀሳብ የያዘ ይመስላል **የሚመስለው የውሉ ግብ ህጋዊ፣ ሞራለዊ፣ የሚቻል እና ግልጽ መሆን እንዳለበት** የሚወስን ቢሆንም 3316 የሚናገረው ስለ ህጋዊነት እና ስለ መልካም ተግባር ብቻ ነው

Q. ውሉ የሚቻል እና ግልጽ ባይሆንስ ?

# ግልግል በፍርድ ቤት ክስ ከተመሰረተ በኋላ ይሠራል?

- በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 275 Compromise በፍርድ ቤት ክስ ከተመሰረተ በኋላም ይሠራል፣
- ተዋዋይ ወገኖች የስምምነት/ Compromise ጥያቄውን በሙሉ ወይም በከፊል (እንደ ወጪ ኪሳራ፣ **የጉዳት ካሳ እና አፈጻጸም የመሳሰሉ 276 ስር ያሉ ተጨማሪ ጉዳዮችን ጨምሮ**) የማቋረጥ እና ከስምምነት ላይ የደረሱበትን ጉዳይ በራስ የመጨረስ መብት ይሰጣቸዋል፣
- በፍርድ ቤት ፊት ክስ ከተመሰረተ በኋላ **በሁለት የተለያዩ መንገዶች ስምምነት ሊደረግ ይችላል፡-** **<u>አንደኛው</u>** በፍርድ ቤት ክርክሩ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ወቅት **<u>ሌለኛው</u>** ደግሞ ከፍርድ ቤት ውጭ ነው
- በሁለቱም መንገዶች የስምምነቱ ይዘት ከ Art 276 (1) ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲቀረጽ ይመከራል

## የዕርቅ ወይም የግልግል ስምምነት ሊይዙ የሚገባቸው ጉዳዮች/ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.276

- ነገሩ የቀረበበትን ፍርድ ቤት ስምና የሚያስችልበትን ቦታ፣

- የክሱን አርእስትና የመዝገቡን ቊጥር ፣

- የተከራካሪ ወገኖች ስም ልዩ መግለጫ የመኖ ሪያ ቦታና መጥሪያ የሚላክበትን አድራሻ

- የእርቁ ወይም የግልግሉ ስምምነት የሚመለከተ ውን ፍሬ ነገር መግለጫ መያዝ ይኖርበታል

❑ የዕርቁ ስምምነት በተጨማሪ የካሣ ንና የኪሣራን አከፋፈል እንዲሁም

# EFFECTS OF CONCILIATION

- After you get in to the proceeding, there are two possible outcomes;
- መስማማት/አለመስማማት/compromise or non conciliation
- በስኬት ከተጠናቀቀ እና ተዋዋይ ወገኖች የጉዳዩ መጨረሻ እና የስምምነት ውጤት በሆነው ነገር ላይ ከመግባባት ከደረሱ **(e.g. res judicata) will apply**

# C) MEDIATION/ CONCILIATION

# MEDIATION – ዕርቅ

- ዕርቅ ማለት አስታራቂ ሚባል ገለልተኛ ወገን አጋዥነት በተደራዳሪ ወገኖች ነፃ ፈቃድ መሰረት ግጭትን ለመፍታት የሚካሄድ ድርድር ነው፣
- አደራዳሪው ተደራዳሪ ወገኖችን ለማገዝ የሚችስል ሚና ይኖሮዋል እንጂ አስገዳጅ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የለውም
- But may advise on or determine the process of mediation
- May be undertaken voluntarily, under a court order, or subject to an existing contractual agreement.

# CONCILIATION/ዕርቅ

- እንደአጠቃላይ **Conciliation / "ዕርቅ"/** ማለት ተዋዋይ ወገኖች በሚመርጡት ሶስተኛ ወገን አጋዥነት ከውል ወይም ከውል ውጪ በሚመነጭ ሕጋዊ ውጤት ባለው ጉዳይ ላይ በክርክር ሂደት ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችልን አለመግባባት ለመፍታት የሚያከናውኑት ሂደት ነው፣
- ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን በጽሁፍ በማድረግ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ስምምነታቸውን ሊገልጹ ይችላሉ፤
- ስምምነታቸው ውጤት የሚኖረው በተዋዋይ ወገኖች መካካል ብቻ ይሆናል

**Art. 2(9), 54 of Procl. 1237/2013/** የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሰራር ሥርዓት አዋጅ

# CONCILIATION/ዕርቅ

**Art. 3318 – Appointment of Conciliator /አስታራቂ ስለመምረጥ**

(1) ተዋዋይ ወገኖች ላንድ ሦስተኛ ሰው እንዲያስታርቃቸውና ቢቻልም በመካከላቸው አንድ ግልግል እንዲያደርግላቸው ሥልጣን ሊሰጡት ይችላሉ ።

(2) **በተዋዋይ ወገኖች፣ጥያቄ አስታራቂው፣ባንድ ፤ ድርጅት ፤ ወይም ፤ ባንድ ሦስተኛ ፤ ወገን ሊመረጥ ይቻላል ።**

(3) አስታራቂ ፤ ሆኖ ፤ የተመረጠው ሰው፣ይኸንን ፤ ሥራ ለመቀበል ' ወይም፣ ላለመቀበል ፤ ነጻነት 'አለው ።

*[Art. 58 of*

# ROLE OF A MEDIATOR

- ለዕርቁ የሚያመች ቦታ የመምረጥ፣
- ምስጢር መጠበቅ፣
- ተደራዳሪዎችን ማገዝ፣
- ተደራዳሪዎች ከጠብ እንዲቆጠቡ ማድረግ፣
- ተደራዳሪዎች ስሜት ውስጥ ሲገቡ እረፍት መውሰድ/ለየብቻ ማናገር፣
- አስታራቂ ሁሌም ግልጽ፣ ታማኝ እና ሀቀኛ መሆን ይኖርበታል

# በዕርቅ ውል ላይ ሊሰፍሩ የሚገቡ ነጥቦች

- የተደራዳሪዎች ሥም
- የአስታራቂ አመራረጥ ሥ/ሥ
- ከአስታራቂ ጋር የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩን መለየት
- የእርቅ ሥርአቱ በቅን ልቦና እንደሚካሄድ መግለጽ
- በዕርቅ የመጨረስ ስልጣን የተደራዳሪዎች መሆኑን
- አስታራቂው የተሰጠውን ስልጣን ብቻ እንደሚጠቀም
- የሚስጥር ጠባቂነት ግዴታ መጨመር
- አስታራቂ በእርቁ ሂደት የተገኘውን መረጃ እንዲሰጥ እንደማይገደድ
- የዕርቅ ሂደት የሚቋረጥበት ጊዜና ሁኔታ
- የዕርቅ ስምምነት በጽሁፍ መሆን እንዳለበት
- አስታራቂውን ከሃላፊነት ነጻ የሚያደርግ አንቀጽ አለማስገባት
- የአስታራቂውን ድካም ዋጋ፣ የሂደቱ ርዝማኔና ወጪዎች መግለጽ
- የተደራዳሪ ወገኖች ስምና ፊርማ
- የአስታራቂው ስምና ፊርማ፣ ቀን፣ ወር፣ ዓ/ም

# የእርቅ ሂደት መሠረታዊ ደንቦች፡-

- አንድ ተደራዳሪ ወገን ሲናገር ሌላኛው ማዳመጥ
- ተደራዳሪ ወገንን ከማጥቃት መቆጠብ
- ተደራዳሪዎች በዬትኛውም ጊዜ ሂደቱን ማቋረጥ እንደሚችሉ ማሳወቅ
- ዋናው ጉዳይ ለተደራዳሪዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠር ..ወዘተ

# CONCILIATION/ዕርቅ

## Art. 3319 – Duties of Parties /C.C

(1) ተዋዋይ ወገኖች ለሥራው አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም መረጃዎች ለአስታራቂው መስጠት አለባቸው

(2) የአስታራቂውን ተግባር የበለጠ ከባድ ወይም የማይቻል ከሚያደርገው ከማንኛውም ድርጊት ይቆጠባሉ

# Q. WHEN TO TERMINATE MEDIATION PROCESS?/የዕርቅ ሂደት መቼ ሊቋረጥ ይችላል?

# የዕርቅ ሂደት ሊቋረጥ የሚችለው:-

- አንዱ ወገን ሽምግልናን/እርቁን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆነ፣
- አንዱ ወገን ለመታረቅ የሚስማማው በነጻ ምርጫው ሳይሆን ሌላውን ወገን በመፍራት መሆኑን ካመላከተ፣
- የስምነቱ መነሻ በልጆች ላይ በሚደርስ ጥቃት ወይም በወሲባዊ ወሲባዊ ጥቃት መነሻ ከሆነ ፣
- ተዋዋይ ወገኖች መራራ ስሜት ውስጥ መሆን እና ግጭት ውስጥ በመሆናቸው ስሜታቸውን ባለመቆጣጠር ትክክለኛውን የሚጋጩበትን ነገር ለመለየት አዳጋች ሲሆን፣
- አስታራቂው የተፈጠረው ነገር ህገወጥ ነው ብሎ ሲያምን

<u>ለምሳሌ፡-</u> በእርቁ ሂደቱ የታክስ ስወራ/**tax evasion**/ ወይም የጤና እና የደህንነት ጉዳዮችን በመጣስ የተፈጸሙ ነገሮች መኖራቸው ሲታወቅ የእርቁን ሂደት ማቆም ያስፈልጋል

# CONCILIATION/ዕርቅ

**Art. 3320 & 3321 – Duties of conciliator**

(1) የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አስታራቂው ተዋዋይ ወገኖች ሃሳባቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲገልጹ እድል ይሰጣቸዋል

(2) የስምምነት ውሎችን ያዘጋጃል ወይም ምንም ሊደረስበት ካልቻለ የእርቅ ስምምነት ሰነዶችን ለተዋዋይ ወገኖች ያስተላልፋል

(3) በ ውሉ ውስጥ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ **ወይም** ከተሾመበት ቀን ጀምሮ **በ 6 ወራት** ውስጥ ተግባራቱን መፈጸም አለበት

(4) አስታራቂው ያለ ስምምነት መጠናቀቁን የሚገልጽ ጽሁፍ ካላዘጋጀ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች ይህ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ወደ ፍርድ ቤት መቅረብ አይችሉም

# CONCILIATION/ARAARA/ዕርቅ

**Art. 3322 – Power of Conciliator**

(1) conciliator's/የአስታራቂው ስልጣን በጠባበ መተርጎም አለባቸ

( 2)ተዋዋይ ወገኖች አስታራቂው ባዘጋጀው የመስማሚያ ቃሎች ለማረጋገጥ **በጽሁፍ በግልጽ** ግዴታ ካልገቡ በስተቀር በስምምነት ውል አይታሰሩም

Art. 3323 – Expenses and remuneration/የአስታራቂው ወጪና ክፍያ

( 3)አስታራቂው ስራውን ለመወጣት ያወጣውን ማንኛውንም ምክንያታዊ ወጪ ተመላሽ ይደረግለታል

( 4)በሌላ መልኩ ስለክፍያው **በግልጽ** ካልተስማማ በስተቀር ክፍያ የማግኘት መብት አይኖረውም

# MEDIATION APPROACHES:-

- As Ury, Brett, and Goldberg (1988) have suggested, they may work through:

i. ***Power-Based Approaches – Mediator influencer***/በኃይል ላይ የተመሰረተ –አስታራቂ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሚሆንበት/

ii. ***Rights-Based Approaches* – mediator legal expert**/በመብቶች ላይ የተመሰረተ – አስታራቂ የህግ ባለሙያ የሆነበት

iii. ***Interest-Based Approaches* – mediation process expert**/በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ አቀራረቦች – የሽምግልና ሂደት በባለሙያ

iv. ***Normative Approaches – Mediator appeals to fairness***/መደበኛ አቀራረብ – አስታራቂው ፍትሃዊነት የሚያተኩርበት

v. ***Manipulation-Based Approaches – Mediator's indirection***/በእውቀት መምራት- አስታራቂ አቅጣጫ ማስቀመጥ

# MODELS OF MEDIATION

1. *Facilitative Mediation* model/አመቻች ሽምግልና

2. *Transformative mediation* model/ ተለዋዋጭ ሽምግልና- ተዋዋዮች ግጭታቸውን እንዲፈቱ በማብቃት ስራ ላይ ያተኩራል

*3. Court-Connected Mediation* model/ከፍርድ ቤት ጋር የተያያዘ ሽምግልና

# 1. FACILITATIVE MEDIATION (FM)/ አመቻች ሽምግልና

- የአሸማጋዩ ተግባር የግራ ቀኙን ግንኙነት ማመቻቸት እና ተዋዋይ ወገኖች የራሳቸውን ውሳኔ እንዲወስኑ ማበረታታት ነው፡፡
- FM የአሸማጋዮች **በክርክሩ የውስጥ ጉዳይ/merits/ ላይ ምክር አይሰጡም ወይም ህጋዊ መረጃ አይሰጡም፣**
- አስታራቂው ምክሮችን አይሰጥም ወይም ውሳኔ አይሰጥም
- የፓርቲዎች ራስን በራስ የማስተዳደር/autonomy/ እና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን ይደግፋል፣
- ለፈጠራ እና ለወደፊቱ በሚጠቅሙ መፍትሄዎች እድሎች ይኖሩታል
- The issues comprise legal and non-legal elements

# 2. TRANSFORMATIVE MEDIATION (TM)/

በመብቶች ላይ የተመሰረተ

- በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖችን ለማብቃት እና አንዳቸው የሌላውን ፍላጎት እና ጥቅም እንዲያውቁ ለመርዳት ያለመ የክርክር አፈታት ሞዴል ነው፣
- TM ግጭት የግንኙነቶች ብልሽት ነው በሚለው ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሰዎች የግንኙነታቸውን ጥራት ሊለውጡ ይችላሉ
- ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባታቸውን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ በተሻለ ሁኔታ መወሰን ይችላሉ በሚለው ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው
- It is *process* focused not outcome፣
- TM *therapeutic* mediation/የሕክምና ሽምግልና/ በማለት ይጠሩታል ይህም ግንኑነትን የማከም ዕድል አለው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው
- TM = changing the quality of conflict interaction

# 3. ከፍርድ ቤት ጋር የተያያዘ ዕርቅ /Court-Connected/court-annexed Mediation model?

## የፍርድ ቤት መር ዕርቅ እንደ ተለመደው የፍርድ ቤት ሂደት ተመሳሳይ ሂደትን መከተል አለበት?

## ከፍርድ ቤት ጋር የተያያዘ ዕርቅ /Court-Connected/court-annexed Mediation model

- ከፍርድ ቤት ጋር የተያያዘ ዕርቅ በፍርድ ቤት አስተባባሪነት በቅድመ ሙግት ደረጃ /pre-trial stage/ያለን ጉዳይ ፍ/ቤት ክርክሩ በሰላማዊ መንገድ እልባት ማግኘት ይቻል እንደሆነ እንዲመረምሩ እድል የሚሰጥበት መንገድ ነው
- Civil matters such as **labor, family, commercial and succession cases are subjected to mediation** before going to the trial stage at court.
- There are **mediation centers in five divisions of federal first instance court and 1 in Federal High Court**

# D) Arbitration [ሽምግልና/ የግልግል ዳኝነት]

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት]

- ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቶቻቸውን በግልግል ዳኝነት በሚሰጥ ውሳኔ ለመፍታት ተስማምተው ጉዳዮቻቸውን ለ3ኛ ወገን የግልግል አካላት የሚያቀርቡበት ስልት ነው፣
- አስቀድመን ካየናቸው የግጭት አፈታት ዘዴዎች የላቀ ተቀባይነት ያለው፣
- የግልግል ዳኝነት ተመራጭ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች መካከል በባለጉዳዮች ዘንድ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችል ውሳኔ መስጠት የሚያስችል ስርዓት ከመሆኑም በተጨማሪ በአሠራሩ ከፍ/ቤቶች ሥራ አካሄድ ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ የህግ ስርአት በመሆኑ ነዉ፣
- የግልግል ዳኛው ምርጫ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ባለው ልዩ የሙያ እውቀት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል

ለምሳሌ፡- መሐንዲስ ወይም የሂሳብ ባለሙያ W

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት]

## Art. 3325 – Definition/C.c

(1) **የግልግል ስምምነት ማለት ተዋዋ ወገኖች ያንድ ክርክርን ውሳኔ ለአንድ የዘመድ ዳኛ/Arbitrator/ ለሆነው ለአንድ ሦስተኛ ሰው አቅርበው የዘመድ ዳኛው /Arbitrator/ በውል/ በሕግ አግባብ መሠረት ይኸንኑ ክርክር ለመቍረጥ የሚያደርገው ውል ነው**

(2) **Arbitrator/የዘመድ ዳኛው በሕግ በኩል ነገሩ የሚያስከትለውን ውጤት ሳይወስን አንድ የተለየ ጉዳይን ብቻ እዲንዲያረጋግጥ ሊመረጥ ይችላል**

## Art. 2(1) – Arbitration Agreement

**"የግልግል ዳኝነት ስምምነት" ማለት ከውል ወይም ከውል ውጭ ባሉ ሕጋዊ ግንኙነት ለፈጠር የሚችልን ወይም የተጠጠረን አለመግባባት <u>በሙሉ ወይም በከፊል</u> በግልግል ዳኝነት ለመፌታት የሚፈፀም ስምምነት ነው**

[የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሰራር ሥርዓት አዋጅ ቁ.1237/2013 ]

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

- **"የግልግል ዳኛ" ማለት በተዋዋይ ወገኖች ወይም በሦስተኛ ወገን የሚሰየም ገለልተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው** See Art. 2(6) of Procl. 1237/2021

- **"የግልግል ዳኝነት ውሳኔ" ማለት አለመግባባቶችን ለመፍታት በቋሚነት በተደራጀ የግልግል ተቋም ወይም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በጊዜያዊነት በሚቋቋም የግልግል አካል የሚሰጥ ውሳኔ ነው**

**See also Art. 2(2) of Procl. 1237/2021**

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

**Art. 8 – Arbitration Agreement and Litigation/**የግልግል ዳኝነት ስምምነት እና በፍርድ ቤቶች ስለሚቀርብ ክስ

1) በአንድ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ውስጥ በሚወድቅ አለመግባባት ላይ ለፍርድ ቤት ክስ ሲቀርብ እና ተከሳሹ **በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ** የግልግል ዳኝነት ስምምነት ያላቸው በመሆኑ በዚያው አግባብ መታየት እንዳለበት **ተቃውሞውን ካቀረበ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ መሠረት ጉዳያቸውን እንዲጨርሱ ሊያሰናብታቸው ይገባል**

2) ሆኖም የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ **የማይፀና ወይም ተፈፃሚ የማይሆን** በሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ይችላል፡

[Procl. 1237/2021]

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት]

3) የተጠቀሰው ክስ በፍረድ ቤት በሂደት ላይ መሆኑ ጉባኤው የግልግል ዳኝነቱን ጎን ለጎን ከመጀመር፣ ሂደቱን ከመቀል እንዲሁም የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ከመስጠት አይከለክለም

4) የግልግል ዳኙት ስምምነቱን መኖር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አለማንሳት የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን ቀሪ እዲሆነ ያስቆጥረዋል

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

Art. 3328 – Arbitration Clause/የግልግል አንቀጽ

(1) በነባር ክርክር/*Existing* dispute

(2) በወደፊት ክርክር /*Future* Dispute ላይ ሊሆን ይችላል

(3) የወደፊት አለመግባባት ከኮንትራት ወይም ከሌላ የተለየ የህግ ግዴታ መነሳት አለበት

(4) የግልግል ዳኞች ስልጣን በጠባቡ ይተረጎማል

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

# Art. 6: Forms of Arbitration Agreement

(1) Shall be in **Writing**

(2) Contents **recorded**, **signed by all parties** and **two witnesses** – even when agreed orally/sign/conduct

(3) AA via **electronic** media shall be deemed to be concluded at a place where the **offeree accepts** the agreement

[Procl. 1237/2021]

# Art. 7: Non-Arbitrable Cases

(1) Divorce/ፍቺ,adoption/ጉዲፈቻ, guardianship/አሳዳሪነት, tutorship/ሞግዚትነት and succession cases/የውርስ ጉዳዮች

(2) Criminal Cases/ የወንጀል ጉዳዮች

(3) Tax Cases

(4) Judgement on Bankruptcy/መክሰር

(5) Decision on dissolution/መፍረስ of business organizations

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

6) All ***land*** cases including lease

***7) Administrative Contracts*** – unless permitted?

8) Trade competition and consumer protection/የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ጉዳይ

*9) Administrative disputes* specifically entrusted such bodies/በሕግ የሚመመለከታቸው አስተተዳደራዊ አካላት በተሰጠ ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ አስተዳደራዊ አለመግባባቶች እና

*10) Other cases* that is not arbitrable under the law

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

**Appointment of arbitrator/የግልግል ዳኞች ስለመሰየም**

(1) *By the parties*: ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞቹን ብዛት በስምምነት መወሰን ይችላሉ፤ ሆኖም የዳኞቹ ብዛት ጎዶል ቁጥር መሆን አለበት፡

( 2) ተዋዋይ ወገኖች የዳኞቹን ብዛት በስምምነት መወሰን ያልቻሉ እንደሆነ የግልግል ዳኞች ብዛት ሦስት ይሆናል፡ (Art. 3331 c.c) and *See Art. 11 (1)&(2) of Procl. 1237/2021*

(2) *By the court*: appoint **odd** number of arbitrators, in turn they shall appoint a president of **the arbitral tribunal** or where they fail to do so – the court appoints. **(Art, 3332)**

*See Art. 12(3) of Procl. 123/2021*

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art- 3334 – Time-limit

(1) Where the other **party or arbitrator fails to appoint** ***within 30 days*** – the FICourt shall appoint such arbitrator – **no appeal** shall lie from

*See Art. 13(3)(b) of Procl. 1237/2021*

( 2) የጊዜ ገደቡ ማስታወቂያው/notice በትክክል ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው

(3) *Modification* to these rules may be provided in the **arbitral submission**.

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art- 3336 – Replacement

(1) Refuses his appointment, dies, incapable or resigns

(2) ከስልጣኑ መሻሻር/Disqualified or removed

(3) **The death of the parties** shall not terminate it – unless otherwise agreed

*[See Art. 17 of Procl. 1237/2021]*

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art. 3339 – Who can be arbitrator?

(1) ማንኛውም ሰው ሊሆን ይችላል

(2) ዜግነቱ ከግምት አይገባም See Art. 12(1) of Procl. 1237/2021

(3) የግልግል ዳኛው ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ነፃ መሆን አለበት

(4) የግልግል ዳኛ ነጻ፣ ገለልተኛ እና የዘርፉ ባለሙያ መሆን አለበት

See Art. 12(5) of Procl. 1237/2021

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

**Art. 13 – Rights and Obligations of Arbitrators**

(1) ማንኛውንም የጥቅም ግጭት ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት

(2) ስያሜውን/ሹመቱን በጽሁፍ መቀበሉን ማሳወቅ አለበት

(3) ለአገልግሎቱ ክፍያ የመቀበል መብት አለው

(4) አላስፈላጊ የግልግል ሂደት መዘግየትን መከላከል አለበት

(5) የቀድሞ ጠበቃ፣ ዳኛ፣ አማካሪ፣ አስታራቂ የነበረ **የግልግል ዳኛ መሆን አይችልም**

(6) አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖችን በተናጠል አያነጋግርም

(7) ከፓርቲዎቹ ምንም አይነት ስጦታ መቀበል የለበትም

*[Procl. 1237/2021]*

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

**Art. 3340 - Grounds of disqualification/ከስልጣን መነሳት**

(1) ዕድሜው ያልደረሰ ወይም በፍርድ ቤት የተፈረደበት፣አእምሮ ጤናማ ያለመሆን/የታመመ ወይም መጥፋት ወይም ተግባራቱን በትክክል መወጣት አለመቻል

( 2) በገለልተኛነቱ ወይም በነጻነትነቱ ላይ ጥርጣሬ በሚፈጠርበት ጊዜ– *[Art. 14(1) of Procl. 1237/2021]*

( 3) አንድ ወገን ራሱ በመረጠው ዳኛ ወይም በምርጫው ሂደት በተሳተፈበት ዳኛ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ የሚችለው ዳኛው ከተመረጠ በኋላ በሚያውቀው ምክንያት ብቻ ነው –*Art. 14(2) of Procl. 1237/2021*

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art. 3343 – Removal/መሻር

ዕርቁን ለማካሄድ የተስማማ የግልግል ዳኛ ግዴታውን ለመወጣት ያለ በቂ ምክንያት/ያለአግባብ/ የሚያዘገይ ከሆነ በስምነት አሊያም አስድሞ ስምምነት ከሌለቸው ስለመዘግየቱ ከተዋዋዮቹ አንዱ ለፍ/ቤት ሲያሳውቅ ፍ/ቤቱ የግልግል ዳኛውን ሊያነሳ ይችላል/ *No appeal shall lie from*].

*[See: Art. 16(1)(2) of Procl. 1237/2021]*

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art. 18 - Arbitration Centers/AC

(1) AC can be established by gov’t or pvt. persons

(2) Federal MoJ/ፍትህ ምንስቴር supervise, issue and renew licenses for ACs

(3) Recognizes existing ACs

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

**Art. 5: Court Interference Prohibited**

**ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ ውስጥ ከተደነገገው በስተቀር በግልግል ጉዳዮች ላይ ጣልቃ አይገባም.**[*Procl. 1237/2021*]

***Art- 3335 – Equality of Parties***

**የግልግል ዳኝነቱ ሁለም ተዋዋይ ወገኖች እኩል የመስተናገድ፣ ጉዳያቸውን የማቅረብ እና የመሰማት መብት ሊሰጣቸው ይገባል።**

*See Art. 12(5)&28 of Procl. 1237/2021*

# Art. 29: Rules of procedure

(1) Equal treatment of parties

(2) Rules of procedures by parties

(3) Rules of procedures by the tribunal

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art. 31 Commencement /አመጀማመር

(1) ማንኛውም የግልግል ዳኝነት ጥያቄ የተቀበለ ሰው በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት

(2) አንድ ፓርቲ በመረጠው ሰው ወይም በጠበቃ በግልግል ሊወከል ይችላል

(3) የግልግል ዳኝነት ጥሪ በአካል፣ በስራ ቦታ፣ በዋና መኖሪያ ቤት፣ በኢሜል ወዘተ ይቀርባል

(4) ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ በሌለበት ይሰማል/ heard *ex-parte*

# Art. 39 – Confidentiality

በህግ ወይም በስምምነት ካልተፈቀደ በስተቀር የፍርድ ሂደቱ እና የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በሚስጥር ይጠበቃል።

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

**Art. 44 – Form, Content and Effect of Arb Award/**የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ፍርም፣ ይዘት እና ውጤት

(1) በጽሁፍ መሆን እና በግልግል ዳኞች መፈረም አለበት

(2) ለውሳኔው መሰረት የሆነው ምክንያት መመዝገብ አለበት

(3) በ15 ቀናት ውስጥ ለፓርቲዎች የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሳቸው ይደረጋል

(4) ማንኛውም በግልግል ዳኝነቱ የሚሰጥ ውሳኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ አስገዳጅነት ይኖረዋል/res judicata ተደርጎ ይቆጠራል።

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art. 48 Objection against Arb Award/ውሳኔ መቃወም

(1) A 3rd party whose right has been affected by AA may *submit objection within **6o days*** from the date he become aware of the award

(2) The provisions of the Civ. Pro. Cd regarding objection of judgement applies

# ARBITRATION ሽምግልና/የግልግል ዳኝነት

## Art. 49 and 50 – Appeal & Setting Aside AA

(1) የግራ ቀኙ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የትኛውም በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ አይቀርብም

(2) በተቃራኒው ካልተስማሙ በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለበት ነጥብ ላይ የሰበር ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል

(3) *Memorandum of appeal shall be filed with in* ***60 days***

(4) *Civil Pro Cd regarding appeal applies*

- ***lack of legal capacity****, Arb agreement become* ***null and void, he has not given proper notice****,* ***arbitrators not impartial/dependent****,* ***the matter is non-arbitrable****,* ***its recognition affects public morality****,* ***or national security***

# ሽምግልና የሚከተሉ ነጥቦች ይገልጹታል

- በተደራዳሪዎች ነጻና ሙሉ ፈቃድ የሚደረግ
- ለተደራዳሪ ወገኖች የአካሄድ ነጻነት የሚሰጥ
- ሽማግሌዎች ነጻና ገለልተኛ መሆን
- የሽምግልና ሥርዓት በሽማግሌው የአካሄድ ስርአት የሚመራ መሆኑ
- ሽማግሌዎች ፍትህና ርትዕ ተከትለው መስራት እንዳለባቸው
- ሽማግሌው የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ ሙኖሩን
- ከሌሎች አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ግልጽ አካሄድ ያለው በፍርድ ቤት አካሄድ አይነት እንዲመራ ይጠበቃል.. የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/አንቀጽ - 317

# E) **HYBRID SYSTEM**

# **ውህድ ሥርዓት**

# COURT-CONNECTED ADR

- It is referred to variously as "court-connected", "court-related", "court-based" or "court-annexed" mediation
- Mediators/arbitrators ሸማግሌዎች፣ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤት ሬጅስትራሮች እና በቅርቡ ደግሞ የተካተቱት ተባባሪ ዳኞች አብዛኛውን ጊዜ በህጋዊ መንገድ ይወከላሉ

# COURT-CONNECTED ADR

1) የፍ/ሥ/ሥ/አንቀጽ - 319(2) በዘመድ ዳኝነት የግጭት አፈታት ሥርዓት ያሸነፈው ሰው ለፍ/ቤት በማመልከት እንዲጸድቅለት መጠየቅ ይችላል፡

2) ፍ/ቤቶች በፍ/ቤት ሂደት ላይ ያለን ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በአማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድን እንዲከተሉ ሊያበረታቱና ሊያመቻቹ ይችላሉ፡፡ የፍ/ብ/ሕ/አንቀጽ 274-277 ይሄንን ይደነግጋል፡

# COURT-CONNECTED ADR

1) ፍ/ቤቶች የፍች ጥያቄ ላይ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ጉዳዩ በእርቅ ከዚያም በሽምግልና ለመፍታት ጥረት እንዲያደርጉ የተሻ/የቤ/ሕ/አ/82 እና 119 ያስቀምጣል፡፡

2) የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.1156/2011 አንቀጽ 144 በእርቅ ጉዳዩን መፍታት ካልተቻለ በግልግል ዳኝነት መፍታት እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡

# PROFESSIONALS IN ADR

- Mediator
- Policeman
- Public prosecutor/district attorney
- Judge
- Pastor
- Lawyer / legal assistant
- Government
- Supervisor
- Referee / arbiter
- Ombudsman
- Manager
- (Financial) adviser
- Coach
- Emergency workers
- Psychologist
- Physicians
- Social worker

# በወንጀል ጉዳዮች የእርቅ አፈፃፀም

# ዓላማው፥-

- በእርቅ ማለቅ የሚችሉ ወንጀሎችን የወንጀል ምርመራ ከመጣራቱ በፊትም ሆነ ምርመራከተጣራ በኋላ ወይም ክስ ከተመሰረተ በኋላ ጉዳዩን በእርቅ መጨረሱ ወጪ ቆጣቢ፣ አስተማሪ፣ማህበራዊ ግንኙነት በሰላማዊ መንገድ እንዲቀጥል ማድረግ፣
- በእርቅ የሚያልቁ ጉዳዮችን በተመለከተ ወጥ አሰራር እንዲኖር ማድረግ
- በእርቅ አፈፃፀም ሂደት ባለሙያዎቹ ሊከተሉት የሚገባቸዉን ስነ-ስርዓት በማስቀመጥ እና ግልፅነት ያለዉ አሰራር ለመዘርጋት

# በእርቅ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች

- በወንጀል ህጉ በወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ወይም በሌላ ህግ ዉስጥ በግልፅ በእርቅ ለማለት እንደሚችል የተጠቀሰ ማንኛዉም ወንጀል እና

- ቀለል ያለ ከህብረሰቡ ጥቅም ይልቅ የተበዳዩን ግለሰብ ጥቅም እና ደህንነት የሚመለከቱቱ በመሆናቸዉ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች በእርቅ ለማለቅ ይችላሉ

በወንጀል ጉዳዮች የዕርቅ አፈጻጸም መመሪያ ቁ.1/2012 አንቀጽ 4(1)

# የወንሉ ጉዳይ በዕርቅ ለማለቅ የማያስችሉ ሁኔታዎች፡-

- የዕርቅ ጥያቄዉ የቀረበዉ ወይም የእርቅ ሂደቱ እየተካሄደ ያለዉ በተበዳዩ ወይም በተከሳሹ ላይ በተደረገ ማስገደድ፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማታለል ወይም ሌሎች የባለጉዳዮችን ሙሉ ፍቃድ የሚያጓድሉ ነገሮች የተከሰቱ ከሆነ፣
- በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሆኑ ግዜ እና በእርቅ ለማለቅ እንደሚችሉ በህግ የተደነገጉ እንደሆነ የተከሳሹ ደጋጋሚነት እና ወንጀሉን ከሌላ ወንጀል ጋር ደርቦ የፈፀመዉ ከሆነ ዐ/ህግ አሁን በእርቅ ለመጨረስ ከታሰበዉ ጉዳይ ጋር ያለዉን ግንኙነት አይቶ እርቁን ለመከልከል ይችላል..፣
- የወንጀሉ የይርጋ ጊዜ ማለፍ፣

**አንቀጽ 4(2 እና 3) ፣ እና 5(1)**

# እርቅ ስለሚፈጸምበት ሁኔታና ጊዜ :-

- **የፖሊስ መዝገብ** ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ ባሉት 14 ተከታታይ ቀናት ውስጥ መፈፀም ይኖርበታል፣
- በልዩ ሁኔታ **እርቁን ለመጨረስ ያለስቻለ በቂ ምክንያት ያጋጠመ እንደሆነ እና በመዝገቡ ላይ ሌላ ዉሳኔ መስጠቱ የሚኖረው ጠቀሜታ ያነሰ** ከሆነ ከላይ የተቀመጠዉ የግዜ ገደብ ሳይከበር እርቅ ሊከናወን ይችላል፣
- **ዓ/ህግ ክስ በፍርድ ቤት መዝገብ ካስከፈተ** በኋላ ክስ **በመሰማቱ ሂደት ውስጥ** በቀጠሮ መካከል ባለጉዳዮች ታርቀዉ ወደ ዐ/ህግ መስሪያ ቤት ከመጡና ማመልከቻው በሀላፊዎች ተፈርሞበት  ለፍርድ ቤት ከቀረበ የክስ መስማት የቀጠሮ ቀን ሳይጠብቅ የክስ ሂደቱ የሚቋረጥ ይሆናል፣
- **እንዲሁም ክስ መታየት ከተጀመረ በኋላ ሲሆን** ባለጉዳዮች መታረቃቸውን በችሎት ለፍርድ ቤቱ የሚያመለክቱ ከሆነ በችሎት ያለዉ ዐ/ህግ ከላይ የተመለከተው **የሃላፊ ደብዳቤ ሳያስፈልገዉ** በጉዳዩ ላይ **ሰምምነቱን በመግለፅ** መዝገቡ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል

See **አንቀጽ 5**

# የእርቅ አፈፃፀም ስነ-ምግባር መርሆች፡-

**በህግ የተቀመጡ ሙያዊ የስነ-ምግባር መርሆች እንደተጠበቁ ሆኖ የእርቅ አስፈፃሚዎች በእርቅ ሂደት ዉስጥ የሚከተሉትን የስነ ምግባር መርሆች ሊከተሉ ይገባል፡-**

1. የእርቅ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ባለጉዳዮች ሙሉ ፍቃድ መስጠታቸዉን ማረጋገጥ እና በአካሄዱ ቅሬታ የሌላቸዉ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. በሂደቱ ለባለ ጉዳዮች እኩል የመሰማት መብት መስጠትና በትህትና ማስተናገድ፣
3. መፍትሔ ለመስጠት <u>የተሻለ ጥቅም</u> ከሌለዉ በቀር ባለጉዳዮችን ለየብቻ አለማነጋገር፤
4. በእርቅ ሂደቱ ለወንጀለ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ ከስር መሰረቱ ሊፈታ በሚያስችል መልኩ መግባባት እንዲፈጠር መጣር፤
5. በእርቅ ሂደቱ የተገኙ ወይም የታወቁ ጉዳዮችን በሚስጥር ይዞ መጠበቅ እና ጉዳዩ በእርቅ ማለቅ ካልቻለ በመዝገቡ ላይ እንደ ማስረጃ አለመጠቀም::

See **አንቀጽ 8**

# የእርቅ አስፈፃሚዎች ሊከተሏቸዉ ስለሚገቡ አሰራሮችና መርሆች ፡-

- በሁለቱም ወገን ያሉ ባለጉዳዮች ጉዳያቸዉን በእርቅ ለመጨረስ ፍቃደኛ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፤
- ሁለቱም ወገኖች በዐ/ህግ መስሪያ ቤት ወይም በፖሊስ መምሪያ ወይም ጣቢያ ተገኝተዉ ከሆነ መዝገቡ ላይ ማስረጃ መሰብሰብ ሳያስፈለዉ የእርቅ ስራዉ ሊሰራ ይችላል፤ ነገር ግን ተከሳሽ ያልቀረበ ከሆነ ለእርቅ የሚጠራዉ መዝገቡ በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ ብቻ ነዉ፣
- ስለ እርቁ አካሔድ እና የህግ ዉጤት ለባለጉዳዮች በአግባቡ ማሳወቅ
- የእርቅ ሂደቱን ግልፅ ማድረግ፣ በገለልተኛነት መምራት፣ በሂደቱ ያለመግባባት የተደረሰባቸዉን ነጥቦች ለመፍታት እንዲቻል እንደነገሩ ሁኔታ ጣልቃ በመግባት የማስታረት ሂደቱን ማገዝ፣

- በባለሙያ ድጋፍ ባለጉዳዮች ስምምነት ላይ ከደረሱ ይህንን የሚገልፅ ሰነድ ጽፈዉ እና ተፈራርመዉ እንዲያስገቡ በማድረግ መዝገቡን በእርቅ መዝጋት ያስፈልጋል፣
- የእርቅ ስራዉ ከባለሙያ ድጋፍ ዉጭ በራሳቸዉ በባለጉዳዮች ተከናዉኖ የመጣ ከሆነ ዐ/ህግ እርቁ በአመልካቹ **ሙሉ ፍቃድ መደረጉን በማረገገጥ** መዝገቡን በእርቅ መዝጋት ይችላል፣
- የግል አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን መከታተል እንደማይፈልግ በፅሁፍ ከገለፀ ዓ/ህግ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 212 መሰረት መዝገብን ሊዘጋው ይችላል፣
- ከላይ የተጠቀሱትን ሂደቶች ሁሉ የግል ተበዳይ በተወካዩ አማካኝነት ሊያከናዉን ይችላል።

See **አንቀጽ 7**

# እርቅ ስለሚከናወንበት ቦታ፡-

- እርቅ የሚከናወነዉ የምርመራ መዝገቡን ለመወሰን እና ለመመርመር ስልጣን በተሰጣቸዉ ዐህጎች ወይም መርማሪ ፖሊሶች ሆኖ በዐ/ህግ ጽ/ቤት ቢሮ፣ የፖሊስ መምሪያ ወይም ጣቢያ በሚገኝ አመቺ ቢሮ ዉስጥ፣
- አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር ደግሞ ዐ/ህግ ወይም ፖሊስ ለቅርብ ኃላፊዉ በማሳወቅ ለእርቁ አመቺ በሆነ ሌላ ቦታ እርቁን ሊያከናዉን ይችላል፣
- እንዲሁም  ባለጉዳዮች በመረጡት ቦታ በግላቸዉ እርቅ ፈጽመዉ በመምጣት የዕርቅ ማመልከቻ ሊያስገቡ ይችላሉ

See **አንቀጽ 6**

# የእርቅ ስምምነት ስለሚፈርስበት ሁኔታ:-

**በእርቅ የተዘጋ መዝገብ በባለጉዳዮች ላይ አስገዳጅነት ያለዉና የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ ቢሆንም በሚከተሉት ምክንያቶች ፈራሽ ሊሆን ይችላል:-**

- እርቁ የተፈጸመዉ ከባለጉዳዮች በአንደኛዉ ወይም በሁለቱም ላይ **በተደረገ ማናቸዉም ሙሉ ፍቃደኝነታቸዉን የሚሸረሽር/የሚያሳጣ ነገር መኖሩ በማስረጃ ሲረጋገጥ** ወይም **ዐ/ህጉ በነገሩ ካመነበት እና ስለዚሁ ነገር ቅሬታ ሲቀርብ፤**
- በእርቅ ስምምነቱ ላይ **የተገለፁ ወይም የተገቡ ቃሎች መፈፀም ሳይችሉ ሲቀሩ** እና በዚህም የተነሳ **ከተስማሚዎቹ አንዱ እርቅ እንዲፈርስለት የጠየቀ ሲሆን፤**

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች እርቅ ስምምነቱ የሚፈርስ ከሆነ ዐ/ህግ ይህንኑ መዝገብ ላይ እንዲሰፍር በማድረግ በመዝገቡ ላይ ተገቢ የሆነ ዉሳኔ ማስተላለፍ አለበት።

- በማንኛዉም ሁኔታ የእርቅ ስምምነቱን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች የተገኙ ሲሆን እርቁን ለማፍረስ የሚቻለዉ **እርቁ በተፈፀመ በአንድ ወር ግዜ ዉስጥ ማመልከቻ ሲቀርብ ብቻ ነዉ**

See **አንቀጽ 9 & 10**

## ሪፖርት ስለ ማቅረብ እና ተጠያቂነት:-

1. ማንኛዉም በእርቅ የተፈፀመ መዝገብ ለቅርብ ሀላፊ ሪፖርት መደረግ አለበት፣

2. ሪፖርት የተደረገለት ሀላፊ እርቅ ይህንን መመሪያ እና ሌሎች ህጎቹን ባከበረ መልኩ የተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል። የእርቅ አፈጻጸሙ መመሪያዉን እና ሌሎች ህጎችን ያልተከተለ በሆነ ግዜ በነገሩ የተሳተፉ ባለሙያዎች በህግ መሰረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

# Thank You!!